# ግርማ ካሳ  ተው የሚልህ ጠፋሳ!!

**8,18,2015**

ባለፈው ሳምንት ውህደትና አንድነትን የሚጠየፈው መድረክ በሚል ርእስ አጭር መጣጥፍ አስነብበኸን ግርምታ ቢፈጥርብኝም የመጻፍ  መብትህን በማክበር ልዩነትን ከማጉላት በሚል ማለፉን መርጬ ነበር ፥ እነሆ አሁን ደግሞ በቆሙበት የሚረግጡ ሰማያዊና መድረክ በሚል ርእስ  ዲሞክራሲያዊ መብትህን ተጠቅመህ የተለመደውን ገንቢ ሳይሆን አፍራሽ የሚመስል ትችት አስነብበህናል፤ ድርጅቶች ያለባቸውን ድክመት አስወግደው ወደ አንድነት እንዲመጡ አልያም በራሳቸው ጠንክረው እንዲወጡ የሚደረገው ግፊት ተገቢና ወቅታዊም ነው ብዬ አምናለሁ፤በተለይም በሃገራችን ያለውን  በበሄር ላይ ያተኮረ አድጎም ወደዘር ፖለቲካ የተቀየረውን ኣካሄድ አደገኛነት የትላንቱ ዘረኞች አንኩዋን ሳይቀሩ እየተገነዘቡት የመጡ ይመስለኛል፥ብዙዎቻችን ቀደም ሲል መድረክን ስንደግፍ የነበረው አንተንም ጨምሮ የብሄር ተኮር ሲያድግም ዘረኝነት በሂደት እየተወገደ ወደ አንድ የተጠናከረ ፓርቲ ይመጣል በሚል ነበር፤ ከዚህም በተጨማሪ የመድረክ አባል ድርጅቶችም ሆኑ መሪዎቻቸው በየጊዜው በሚናገሩዋቸዉና በሚያስተምሩበት መድረክ ሁሉ በኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ላይ በሃገር ሉኣላዊነትና አንድነት  ከብዙዎቻችን የኣንድነት ሰባኪዎች በላይ የተሻለ የሰበኩ ያስተማሩ መድረክንም ካለበት አደረጃጀት ለመቀየር ቅን ልቦና የነበራቸው ለመሆኑ የምታውቀው ይመስለኛል፥በተለይም አንተ ብቸኛ የፖለቲካ ድርጂት አድርገህ የምትወስደውን አንድነት ወደመሃል ፖለቲካ ተሸጋግሮ በጋራ ጠንካራ ድርጅት ለመፍጠር ከሁለት ኣመት በላይ ሰፊና ጥልቅ ውይይት ተካሂዶ አንድነት የነበረበት መድረክ በምንም መመዘኛው ወያኔ ኢሃዴግን ስጋት ውስጥ የጣለ የተረጋጋና ግልብነት የማይታይበት ነገር ግን የኢኮኖሚ አቅሙ ከወያኔ ኢሃዴግ ጋር የማይመጣጠን ስብስብ ሆኖ ነበር ፤ አንድነት ከመድርከ ሊወጣ የቻለበት ምክንያት አሁን ውንድሜ ኣቶ ግርማ የሰጠህው አስተያየት ያለፈው አንድነትን ከመድረክ ያስወገደው ቡድን ተቀጽላ አስተሳሰብ ለመሆኑ መለስ ብለህ አንደነት ከመድረክ መዉጣት እንዳለበት በተለያየ መንገድ የጫጫርካቸውን ብትመለከታቸው ይጠቅማል ፥ በተለዪም ኣንተና የኣንድነት ደጋፊ ነን የሚሉ የዲኣስፖራው ጥቂት የኣንድነት ሰባኪዎች ውጤት ነው፤ ለዚህም መድረክ አንድነትን ቆልፎ እንዳይንቀሳቀስ ይዞታል የሚል የጠብ ኣጫሪነት ፖለቲካ ውጤት ነው፥አንድነትን ከመድረክ እንዲወጣና በወቅቱ የጫጉላ ሰሞኑን ያከብር የነበረውን ሰማያዊን አንዲቀላቀል የተደረገው የሆይሆይታ ፖለቲካ ስራ ነው፥ በውጤቱም በብዙ መልኩ ጠንካራና ዠንጥላ መልክ የነበረውን አንድነት በገዢው ፓርቲ ተነጥሎ አንዲመታና የድርጀቱም ህልውና ኣደጋ ውስጥ እንዲወድቅ ሆኖኣል፤፤ኣንድነትና ሰማያዊ ካልተዋሃዱ የኢትዮጵያ ኣንድነትና የህዝቦችዋም አኩልነት ሊረጋገጥ ኣይችልም ኣይነት ጩህት ሲሰማ ነበር፥፥

በሃገራችን የዘር ፖለቲካ **ethnic poletics** እንዲጠፋ የምንመን ብዙዎች ነን ፥፥ በርግጥም ኣጥፊ ፖለቲካ ነውና፥፥ ቁምነገሩ ግን መፍትሄወን የምናስቀምጠው በዚያው በምንጠላው ዘረኝነት ቀለበት ውስጥ ነው፥ ወይም የተወሰኑ ክፍሎች ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከቱበት መንገድ መሆን ኣለበት የሚል ውርዴ ኣመለካከት ነው፥ ዘረኝነትን በምንም መልኩ በዘረኝነት ማጥፋት ኣይቻልም ምንጩ ሁዋላ ቀርነትና የድህነት አስተሳሰብ ነው፥ ይህንንም በመጠቀም ጥራዝ ነጠቅ ፖለቲከኞች የፖለቲካ ስግብግብነትና ከውስጥ የሚመነጭ የጥላቻ ፖለቲካ ነጸብራቅ ነው ፤ሰዎች በዘራቸው የሚሰባሰቡት የዘር ፖለቲካ በቀላሉ የሚያድናቸው የሚጠብቃቸው ስለሚመስላቸው ነው፥፥ ሊወገድ የሚችለውም ግለሰቡ በዘሩ ከመጠለል ሊያድነው የሚችል ኣመች ሁኔታ ሲፈጠር ነው፥ የፖለቲካ ምሁራኑም በቀላሉ በዘራቸው ተቀባይነትን የሚያገኙበት ኣትሞስፈር ካለ ይነጉዱበታል፤፤ በሃገራችንም ይህ በሚገባ ታዪቶኣል ፤፤ አንዳንድ ጽንፍ ኣመለካከት ያላቸው ወግኖቻችን የመገንጥል አስተሳሰብ ሰለባ የሆኑት ለዚሁ ነው፥ በሌላ በኩል ያሉ ጽንፈኛ ወንድሞቻችን ደግሞ ኣንድ ሰው ራሱን ኣማራ ነኝ ስላለ ወይም ትግሬ ወዪም ኦሮሞ ወይም የተወለደበትን ብኄረሰብና ከብሄረሰቡ ጋር የተያያዘ የቦታ ስም ከገለፀ ዘረኛ ተደርጎ የሚታይበትም ሁኔታ ኣለ፤ዘረኝነት በዚህ መንገድ ኣይጠፉም

ወይም የተለያዩ ብሄረሰቦችን ማንነት ልዩነትና ኣንድነት ያላቀፈች የተንሳፈፈች ኢትዮጵያ የለችም፥ኢትዮጵያዊነት የነዚህ ስብስቦች ጌጥ ነው፥ወያኔ ኢሃዴግ ይህን ጌጥ ነው ጥላሸት ኣልብሶ በብሄር ጥያቄ ስም ልዩነትን በማራገብ የስልጣን ጊዜውን ለማራዘምና የብሄር ጥያቄ የእኩልነት ጥያቄ መሆኑ ቀርቶ በብሄር ስም ከፋፍለህ ግዛ የሚለውን የ ዘር ፖለቲካ ስር እንዲሰድ ያደረገው፥፥ ለዚህ ደግሞ በስመ ኢትዮጵያዊነትም ሆነ በጠባብ የብሄር ፖለቲካ የተዘፈቁ ሁሉ ለችግሩ ተጠያቂ የሚሆኑት ፥፥

ስለዚህ ወንድም ግርማ ኢትዩጵያዊነት ኢትዮጵያወያን የፖለቲካ ድርጅቶችን መበታተኛና ማጋጫያ ሊሆን አይገባም፥፥ የመድረክ የፖለቲካ ፕሮግራም የኢትዮጵያዊነት ፖለቲካ መገለጫ ነው፥ ሰሞኑንም በመታጥፍህ ላይ የሰነዘርከው ትችት ኣግባብ ያልሆነና ወደውህደት ለመምጣት እንዲያተኩሩ ድርጅቱ የወሰነውን ውሳኔ በተጻረረ መልኩ ኣንድነትን የሚጠየፈው መድረክ በሚል ኣፍራሽ አርእስት የፖለቲካ ጠቀሜታ የሚገኝ ኣይመስለኝም፥

ኣሁን ደግሞ የጫጉላው ጊዜ ያበቃ የመስለውን ሰማያዊን የፖለቲካ ድርጅት መሪውን  ግርማ መምረጥ ኣለበት በሚል ኣይነት ኣስተሳሰብ በድርጅቱ ህልውና ውስጥ ገብቶ አከሌን ምረጡ እከሌን ኣትምረጡ ኣይነቱ ለምትደግፈው ኣንድነትም የጎዳ ፖለቲካ በመሆኑ በሃገር ወዳድ ኣክቲቪስቲነትና በፖለቲካ ድርጂት ኣባልነት መካከል ያለውን መስምር ባናጣልዘው ጥሩ ዪመስለኛል፥ የተገነባውን እያፈረሱ ኣዲስ መገንባት ድምር ውጤቱ ዜሮ ነው፥ መተቸት የዲሞክራሲ መብት ነው ለሚሉ ደግሞ የዲሞክራሲ ትርጉም ቅጥ ኣምባሩ እየጠፋ ያለበት ዘመን በመሆኑና ዲሞክራሲ ስሙን ኣፍራሺነት እየተጫነው መጥቶኣልና ከዚያ ዩሰውረን፥

ወንድሜ ግርማ ሁሉንም ስለምትውቅስ በገንቢ መልኩም እያደነቅኩ እውነት ግን የግለሰብ ብቻ ኣለመሆኑዋን አንደምትረዳለኝ ተስፋ ኣድርጋለሁ

መልካሙን  እመኝልሀለሁ

ቶኩማ    ኣሸና ፊ